በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

## የተሰጠ መግለጫ

*ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም*

## *ለሥርዓት ለውጥ እንዘጋጅ*

*የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፏል። ማህበሩ ለተቋቋመበት ዓላማና ግብ እየሠራ ውጤታማ እንዳይሆን በየጊዜው በተፈራረቁ ገዢ መንግሥታት አፈና ሳቢያ አባላቱ ለእንግልት፣ አመራሮቹ ለሞት ፣ ለእስራት፣ ለስቃይና ለስደት መዳረጋቸው የማህበሩ ታሪክ አካል ሆኖ የሚታወስ ነው። በተለይም በወያኔ /ኢህአዴግ በተፈጸመበት እመቃ ማህበሩ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ህልውናውን አጥቶ እንዲፈርስ መደረጉና በአምባገነኑ ሥርዓት አምሳያ ተጠፍጥፎ የተሠራ ተለጣፊ ማህበር ተፈጥሮ ማየቱ አሳዛኝ ክስተት ሆኗል።*

*ምንም እንኳን ወያኔ/ኢህአዴግ ዕውነተኛውን ማህበር አፍርሶ በራሱ አምሳያ የተፈጠረውን ማህበር ተብዬ ቢያጠናክርም በማስተማር ሙያ የተሰማሩ አብዘኛው መምህራን ማህበራቸውን ከአገዛዙ መዳፍ ፈልቅቆ ለማውጣት በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተቃውሟቸውን ማሰማታቸውና ጥያቄዎችን ማንሳታቸው አልቀረም። በቅርቡ የትምህርት ሚኒስቴር ከብሪትሽ ካውንስል ጋር በመተባበር በአዳማ(ናዝሬት) ከተማ በአዳማ ራስ ሆቴል ለእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ለ10 ቀናት የሚቆይ ስልጠና በሰጠበት ወቅት ከአበል ክፍያ ጋር በተያያዘ በተፈጠረ አለመግባባት የሥልጠናው ሂደት ሳይጀመር ተጠናቀቀ ለማለት በሚስያችል መልኩ በንትርክና በጭቅጭቅ አልፏል።*

*ለዚህ አሳዛኝ ውዝግብ መንስኤ ደግሞ ከወቅቱ የኑሮ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘበ የውሎ አበል አከፋፈል ሲሆን ይህም ዝቅተኛው አንድ መቶ ሃያ አምስት ብር፣ ከፍተኛው አንድ መቶ ዘጠና ሶስት ብር ነው መባሉ ነበር። በዚህ የተነሳ አሳዛኝ ውዝግብ ተፈጠረ።የስልጠናው ታዳሚ መምህራን በትምህርት ሚኒስቴር የስልጠናው አስተባባሪዎች ላይ ትምህርት ሚኒስቴር የወረደ መ/ቤት ነው፣ ተንገታግቷል ፣ ግልምቷል ፣ እስካሁን ያሳካው ትልቅ ስኬት አለ ከተባለ ትምህርት መግደሉና እውቀት አልባ ትውልድ እንዲፈጠር ጠንክሮ መስራቱ፣ አገሪቱን በዕውቀት አልባ ተተኪ ትውልድ ማስቀረቱ ፣ መምህራንን ማደህየቱና ሞራላቸውን ማድቀቁ .... ወዘተ ነው በማለት ተቃውሟቸውን አሰሙ። የስልጠናውም አስተባባሪዎች እንደምንም ተለማምጠውና ሆቴሉ ምሳ እንዲችል ተደራድረው ስልጠናው ቀጠለ። አሰልጣኖቹ እራሳቸው ስሜታቸው ተነክቶ ስለነበር ከስልጠናው ተሳታፊዎች የርስ በርስ የልምድ ልውውጥ ውጭ ይህ ነው የሚባል ቁም ነገር ሳያስጨብጡ ስልጠናው እጅ እጅ ብሎ ሰንብቶ የማጠናቀቂያው ጊዜ ደረሰ። በእለቱም ከትምህርት ሚኒስቴር ተወክሎ የመጣ አንድ ሚኒስትር ዴኤታ ተብዬ ስለመምህሩ ሁኔታ ፣ ወደፊት ለመምህሩ ስለታሰበው የደመወዝ ጭማሪ ከሙያ ማህበሩ ጋር አብረው እየሰሩ እንደሆነ ለመናገር ሲሞክር ሰልጣኞቹ በአንድ ድምፅ ተለጣፊው ኢመማ አይወክለንም ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ከደረጃው ወርዷል፣ ቆም የሚሄድ ውሸት ነው የሚዋሸው በማለት በአንድ ጊዜ ሲጮሁ ሚኒስትር ዴኤታው ደንግጦ የአምስት ደቂቃ የመዝጊያ ንግግር እንኳን ሳያደርግ የውርደት ካባ ተከናንቦ ከአዳራሹ ወጥቶ ለመሄድ ተገዷል።*

*በሌላ በኩል ወያኔ/ኢህአዴግ ከመጭው ምርጫ 2007 ዓ.ም ጋር በተያያዘ የመምህሩን ቀልብ ለመሳብና ድጋፍ ለማግኘት በአምሳሉ ጠፍጥፎ ካቋቋመው የመምህራን ማህበር ተብዬ ጋር ከላይ ታች በመሯሯጥ ላይ ይገኛል። ለዚህም ጥሩ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ተለጣፊው የአማራ ክልል መምህራን ማህበር ካወጣው ባለ 12 ነጥብ የአቋም መግለጫ ( የሁሉም ክልሎች ተለጣፊ መምህራን ማህበር የአቋም መግለጫ አንደሚሆን ይገመታል)ውስጥ፡-*

1. አገራችን ኢትዮጵያ የዜጎቿን ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልባትና ድህነትን ታሪክ አድርጎ ለማስቀረት እየተገበረቻቸው ካሉት ተግባራት አንዱ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ትምህርት ፈላጊ ህፃናት ማዳረስና የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ነው ። በመሆኑም እኛ መምህራን ኃላፊነታችንን በመወጣት ለትምህርት ፖሊሲው ተግባራዊነትና ከግብ መድረስ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን።

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

2. የተፈለገውን የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ እንዲቻል በየደረጃው ያሉ መምህራን የተለያየ የደመወዝ ደረጃና እርከን ተዘጋጅቶ በቆይታ ጊዜና መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተው ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። ለዚህም የክልላችን ት/ቢሮ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን ። ይሁን እንጂ በቆይታ ጊዜ የምናገኛቸው ደረጃ እድገቶች ተግባራዊ ቢሆኑም በየሁለት አመቱ ማግኘት ይገባን የነበረ የእርከን ጭማሪ መቋረጡ በከፍተኛ ት/ት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ 2ኛ ድግሪ ያላቸው መምህራን መሪ ደረጃ ደርሶ መቆም እንዲሁም በአሁኑ ደረጃ እየተከፈለ ያለው ደመወዝ የኑሮ ውድነቱን መቋቋም ያስቻለ አለመሆኑ እንድንቆዝም የሚያደርገን ስለሆነ ፍትሃዊ ማስተካከያና መልስ እንዲሰጥበት እንጠይቃለን።

3. በክልላችን ባሉ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ከአንጋፋ እስከ አዲስ ተቀጣሪ መምህራን ድረስ በስራው ተሰማርተን እንገኛለን። ሆኖም ግን ካለው ኑሮ ውድነት እና ሌሎች ተጫማሪ ምክንያቶች የተነሳ ከፍተኛ አገልግሎት ያላቸው መምህራን በራስ ፈቃድ ጡረታ በመውጣት አዲስ ተቀጣሪ መምህራን ስራቸውን በመልቀቅ የትምህርቱ ስራ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚደርስበት እንደሆነ ከቀረቡት ሪፖርቶች ማረጋገጥ ይቻላል።በመሆኑም መምህራን ተረጋግተው በመስራት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል የክልል ት/ት ቢሮ የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሩ እልባት እንዲሰጠው ትኩረት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ እየጠየቅን ለተግባራዊነቱ ከማህበሩ የሚጠበቀውን ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን።

4. የመኖሪያ ቤት ችግራችንን ለመቅረፍና የቤት ባለቤት ለመሆን እንዲንችል ያቀረብነው ተደጋጋሚ ጥያቄ ጊዜ የወሰደ ቢሆንም የክልላችን መንግሥት የጉዳዩ አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የማስፈጸሚያ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ላይ ይገኛል። መመሪያ ተዘጋጅቶ በመውረዱ ለክልላችን መንግሥት እንደዜጋ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ሆኖም ግን የተዘጋጀው ደንብ የመምህራንን የመከፈል አቅም ያላገነዘበና የገጠር መምህራንና በከተማ የሚኖሩ መምህራንን የለየ በመሆኑ በማህበር ተደራጅተው የቆዩ የቤት ማህበራትን ያላከተተ በመሆኑ የክልል መንግሥታችን ትኩረት ሰጥቶ ደንቡን የማሻሻል ስራ በመስራት የቤት ባለቤት እንድንሆን ያደርግ ዘንድ እየጠየቅን የክልል ት/ቢሮም ከጎናችን ቆሞ እገዛ እንዲያደርግልን የሚለው ይገኝበታል።

*ከተራ-ቁጥር 1-4 የተጠቀሱት የአቋም መግለጫዎችም ሆኑ ሌሎቹ ጠንካራና አስገዳጅ በሆኑ ቃላት ያልታጀቡ ጥያቄዎች ባይመለሱ ማህበሩ ምን ዓይነት ጠንከር ያለ እርምጃ ለመውሰድ እንደተዘጋጀ በአንድም የአቋም መግለጫው አለማመላከቱ ይህን አልኩ ከማለት ባለፈ ተጨባጭ ውጤት ሊያመጣ የማይችል ከንቱ ውዳሴ "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ " ዓይነት ነው።*

*መምህሩ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ በሚገኝበት ፣ የትምህርት ፖሊሲው ትውልድ ገዳይ ተብሎ ከመነሻው ከፍተኛ ተቃውሞ በቀረበበት ፣ የትምህርት ጥራት ከመቼውም ጊዜ በላይ በዘቀጠበት፣ መምህራን ከደመወዝ ጭማሪ ጋር በተያየዘ ያነሱት ጥያቄና ያደረጉት ተቃውሞ በታፈነበት ፣ የአካዳሚ ነፃነት በሌለበት ፣ በዚህም ሳቢያ ልምድ ያላቸው መምህራን በተለያዩ ጊዜያት የማስተማር ስራቸውን እየለቀቁ በሚሄዱበት፣ በአንዳንድ ት/ቤቶች በመምህራን እጥረት የተነሳ የመማር ማስተማር ስራው በተስተጓጎለበት ሁኔታ ባዶ ፕሮፖጋንዳ ከቶውንም ዋጋ የለውም። እንዲሁም መምህራን የመኖሪያ ቤት ለመስራት የወያኔ መንግሥት በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጠውን መሬት ለመግዛትና ቅድሚያ ክፍያ ለመክፈል አቅም ባጡበት ሁኔታና ቅድሚያ ክፍያውም ሃያ ሶስት ሺ ብር በላይ በሆነበት ፣ በጥረታቸው ቤት የሰሩ ጥቂት የማይባሉ መምህራን የመኖሪያ ቤታቸው በአንዳንድ ከተማዎች ሕገወጥ በሚል በላያቸው ላይ እየፈረሰ ባለበት ሁኔታ ማህበር ተብዬው (ተለጣፊው) የተለሳለሰ የይምሰል የአቋም መግለጫ ማውጣቱን መምህራን በመኮነን ተቃውመውታል። ምርጫ ሲደርስ መደለያ ነው በማለት ተለጣፊውን ማህበር አትወክለንም ብለዋል።*

*አምባገነኑ ሥርዓት ሥልጣን ለሕዝብ ላለማስረከብና ሰላማዊ ሽግግር እንዳይኖር መረን በለቀቀ የማንአለብኝነትና የዕብሪት ተግባሩን በከፋ መልኩ እያጠናከረ እንደሆነ ይታያል። የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን ፣ ተማሪዎችንና መምህራንን ፣ አርሶ አደሩን፣ የአካባቢ ሽማግሌዎችን --- ወዘተ አንድ ለአምስት በማደራጀትና በመጠርነፍ በአገሪቱ አንጡራ ሀብት የዘጠና ብር የውሎ አበል በመመደብ ለምርጫ 2007 ዓ.ም ቅስቀሳ ጀምሯል። ትምህርት ቤቶች ከፖለቲካ ተግባር ነፃ ናቸው የሚለውን የራሱን ሕግና ደንብ በመጣስ ልክ እንደ ደርግ ጊዜ የፓርቲ መሰረታዊ ድርጅት ጽ/ቤቶች በየት/ቤቶቹ*

*እየተቋቋሙ የሥርዓቱ ቅጥረኛ ተማሪዎች በዚህ መዋቅር ሰበብ በመማር ማስተማሩ ሥራ ጣልቃ በመግባት በመምህራን ላይ አሉታዊ ጫና መፍጠራቸው ተረጋግጧል። ይህ እንዳለ ሆኖ የመምህራን የመብት ማስከበር ጥያቄና ትግል አላቋረጠም። በደቡብ ክልል በአንዳንድ ት/ቤቶች ¾( ሶስት አራተኛ) የሚሆን ቁጥር ያላቸው መምህራን ለተለጣፊው መምህራን ማህበር ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ አንከፍልም ብለው ማቋረጣቸው ትግሉን አንድ እርከን ከፍ እንዳደረገው የሚያሳይ ሲሆን በሌሎችም ክልሎች ሊቀጥል የሚገባው የትግል ስልት እንደሆነ ይታመናል።*

*በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ መምህራን መብትና ነፃነታቸው ሊከበር የሚችለው ተደራጅቶ በመታገል ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው። በተናጠል የሚደረግ ትግል የሚከፈለውን መስዋዕትነት ከማብዛትና ሁኔታዎችን ከማወሳሰብ በዘለለ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አይደለም። በተለይ አሁን የኢትዮጵያ ጠላቶች ከውጭም ከውስጥም በተባበሩበት ወቅት። ከእንግዲህ ወዲያ ከወያኔ/ኢህአዴግ የሚገኝ የተስፋ ጭላንጭል ባለመኖሩ ለራሱ ዓላማ ማስፈጸሚያ ሲል ለሚያቀርብልን መደለያና ማታለያ ሰለባ መሆንና ሁሌም ይህን ያደርግልናል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው። "ከእባብ እንቁላል እርግብ አይጠበቅም " ። ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑን ያለጥርጥር ማወቅ ይኖርብናል። ያ ባይሆን ኖሮ የጠየቅነውን የመብት ጥያቄዎቻችንን በመለሰ ነበር።*

*ወያኔ/ኢህአዴግ ቃሉን የማያከብር የአገርን አደራ የበላ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ረግጦ የመማርና ማስተማር ነፃነትን ገፎ፣ የመምህሩን ክብር አዋርዶ ፣ ለሆዳቸው ያደሩትን በጥቅማጥቅም ደልሎ አቅፎና ደግፎ በእሳት ረመጥ ላይ የቆመ አምባገነን ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ ይህ የቆመበት የእሳት ረመጥ እየዋለ እያደረ ውስጥ ውስጡን እንደቋያ እየነደደ ራሱንም የሚያነድበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ትውልድን አደንቁሮና እውቀት አልባ አድርጎ በታሪክም በትውልድም ይቅር የማይባል ወንጀል እየፈጸመ በሚገኝ ሥርዓት ላይ ሁሉም ሊነሳ ይገባል። ወያኔ/ኢህአዴግን በቃ ማለት የጊዜው ጥሪ ነው። ለለውጥ ካልተዘጋጀንና የየበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ በቁርጠኝነት ካልተነሳን አደጋው ከዚህም የከፋ ይሆናል።*

*እኛ መምህራን ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ ለጠፋው ሕይወትና ለወደመው ንብረት የወያኔ መንግሥት ተጠያቂ ስለሆነ ለተጎዱ ወገኖቻችን ካሳ እንዲከፍል፣ ለሚነሱ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ እየጠየቅን እንዲሁም ጋዜጤኞችን፣ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎችን በአጠቃላይ ኢትዮጵያን የሕዝቧቿ እስር ቤት አድርጎ የሚገኘው የወያኔ ማፊያ ቡድን ከሰሞኑ ከየመን መንግሥት ጋር በመሆን የግንቦት 7 ዋና ጸሀፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን የየመን መንግሥት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ የዓለም አቀፍ ሕግን በመተላለፍ ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱን፤ በአገሩ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰውን በደል በጥብቅ እንቃወማለን፤ ድርጊቱንም እናወግዛለን። ወያኔ/ኢህአዴግ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን እየጣሰና ሰብአዊ መብቶችን እየደፈጠጠ በስልጣን ላይ ተፈናጦ መኖር ስለማይገባው ኢትዮጵያዉያን በአገር ውስጥም በውጭም ድርጊቱን መቃወም፣ ማውገዝና ለዓለም ሕብረተሰብ ማጋለጥ ይጠበቅባቸዋል።*

*የትውልዱ እጣ ፈንታ ተስፋ ሰጭ ሊሆን የሚችለው አምባገነኑ ሥርዓት ተወግዶ ለሁሉም የምትሆን ዴሞክራሲያው ሥርዓት የሰፈነባት፣ የዜጎች ነፃነት፣ ሰብአዊ መብትና የሕግ የበላይነት የሚከበርባት አገር መገንባት ሲቻል ነው። በመሆኑም ከቀደሙት የትግል ታሪክ ትምህርት ወስደን የለውጥ ሀዋሪያ በመሆን አገራችንን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ በሚደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ሆነን አገራዊና ሕዝባዊ ግዴታችንን እንድንወጣና ለሥርዓት ለውጥ እንድንዘጋጅ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ለመምህራን ፣ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለገበሬዎች ፣ ለወጣቶች ፣ ለሴቶች፣ በአጠቃላይ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥሪውን ያቀርባል።*

*የመምህራን መብት በትግላችን ይከበራል!!*

*ለሥርዓት ለውጥ ቆርጠን እንነሳ !!*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*